# ለዳኮታ ጥንት ማዕከል መልስ

ሲራክ ከሚድ ዎስት

የዳኮታን የጥናት ማዕከል ጽሁፍ ደግሜ ደጋግሜ አነበብኩት። ጽሁፉ ከወጣ ወደ ሶስት ሳምታት ይሆነዋል፡፡ ዳኮታ ያመነበትን በመሰለው መልኩ ማቅረቡን ከግንዛቤ ውስጥ እያስገባሁ ስለ ጽሁፉ የምለው ብዙ ነጥብ ስላለኝ እንዲያዳምጡኝ ወይም እንዲያነቡልኝ እፈልጋለሁ፡፡ ባብዛኛው በጽሁፋቸው በፍጹም አልስማማም፡፡

ጽሁፉ ገና ሲንደረደር የ60ዎቹን ንቅናቄ እንደ ጥፋት በመቁጠር ነው፡፡ **ያኔ የተማሩና የነቁ ተማሪዎች የዛን ጊዜ የጫሩት ጥፋት ከ40 አመትም በሁኣላ ዛሬም ተከትሎናል ይለናል፡፡** የዳኮታ የጥናት ማዕከል የዚያን ትውልድ መስዋእትነት ማስታወስ ያልፈለገ ብሎም ከግማሽ ሚሊዮን በላይ ሕዝብ ለአገሩ ሲል በራሱ መንግስት እንደ ከብት የታረደበትን የነቁ ተማሪዎች <u>ልዩነት ፈጥረው የተራቀቁበት፤የተጣሉበትና የተገዳደሉበት</u> ነበር ብሎ ሊያስተምረን ይደፍራል፡፡ እንዲያውም ዋናውን ጠላታቸውን ደርግን አስቀምጠው እርስ በራሳቸው ሲናቅሩ ነበር ብሎናል፡፡ ዳኮታ አርስ በራሳቸው የሚላቸው ኢሕአፓንና መኢሶንን እንደሆኑ ግልጽ ነው፡፡ ለምን ዳኮታ ስማቸውን መጥራት እንዳላስቻለው አልገባኝም፡፡ **በዳኮታ አባባል መኢሶንና ኢሕአፓ ባንድ ወገን ደርግ ደግሞ በሌላ ወገን ሆኖ የሚካሄድ ትግል እንደነበር ለመተረክ ይዳደዋል**፡ ሃቁ ግን መኢሶንና ደርግ ግንባር ፈጥረው ኢሕአፓን ከምድረገጽ ለማጥፋት ይህ ነው የማይባል ፍጅት እንዳደረጉበት የዳኮታ ምርምራዊ ጥናት አልተገለጸለትም ወይም እያወቁ ለመካድ ነው፡፡

<u>የያኔው ትውልድ ቅራኔ ማቻቻል አቅቶት ነበር</u> የሚል ጽሁፍ በጥናታቸው ውስጥ ተደጋግሞ ተስንዝሯልና እስቲ ስለ ቅራኔ 101 ጥቂት ልበል፡፡ ቅራኔ ፈለግንም አልፈለግን የሚኖር ጉዳይ ነው፡፡ ለውጥም የሚመጣው ቅራኔ ስላለ ነው፡፡ ዳኮታ ቢያንስ ሁለት አይነት ቅራኔዎች ስለመኖራቸው አያውቅም ወይም ቢያውቅም ለመጥቀስ አልፈለገም፡፡ ሊታረቅ ወይም ሊቻቻል የሚችል ቅራኔና ሊታረቁ የማይችሉ የቅራኔ አይነቶች መኖራቸውን ማወቁ ከስህተት ያድነናል፡፡ **ተነጋግረው ልዩነታቸውን ሊፈቱ ሲችሉ እርስ በርሳቸው ሲናቆሩ አብዮቱ ግቡን እንዳይመታ አድርገዋል የሚል ክስ ዳኮታ በያኔዎቹ የነቁ ተማሪዎች በሚለው ክፍል ላይ ይጭናል፡፡** መኢሶንና ኢሕአፓ ልዩነታቸውን ለማርገብ የተደጋገመ ውይይት ማድረጋቸው ይታወቃል፡፡ ልዩነታቸው የከረረ በመሆኑ ማለትም የመኢሶን አቋኣም ሕዝብን የሚጉዳና የማይበጅ ከሆነ ደረጃ ላይ በመድረሱ መታረቅ አልቻለም፡፡ በሰላማዊ መንገድ ልዩነትን ለመፍታት በማይቻልበት ጊዜ የግድ ወደ ሃይል ይገባል፡፡ መኢሶንና ደርግ አንዳችም የኢሕአፓን ልብ የሚሰርቅ መንገድ አልተከተሉም ነበር፡፡ ስልጣኑን ለሕዝብ ለመልቀቅ አልፈለጉም፡፡ ኢሕአፓን በጠላትነት ፈርጀው የመጀመሪያዊን የጥፋት ጥይት የተኮሱበት ደርግ/መኢሶን ነበሩ፡፡

ዳኮታ ኢትዮጵያ ለዛሬው ውርደት የተዳረገችው በደርግ መሆኑን ለማሳነስ ሲመችውም ጥፋተኖቹ የዚያ ትወልድ የነቁ ተማሪዎች (ማለትም ኢሕአፓ) ነው ብሎ ሊያታልል ይከጅላል፡፡ **የትግሉ ሂደት እንዳይቃና የዚያን ጊዜ የነቁ ተማሪዎች አሁንም በድርጅታቸው በመሪነት ላይ ስለሚገኙ ተጽዕኖ ያደርጋሉ በማለት** ከፍተኛ የትግል ተመክሮ ያካበቱትን የትላንት ወጣቶችን የአሁኑን እድሜ ጠገብ መሪዎችን ሲያጣጥል ታይቷል ፡፡ ባሁኑ ጊዜ መኢሶን የለም፡፡ ደርግም የለም፡፡ ያለው ኢሕአፓ ነው ዳኮታን ይክፋውና፡፡ መኖር ብቻ ሳይሆን አሁንም ለኢትዮጵያ አገራዊ ሉኣላዊነትና ለሕዝብ አንድነት ያለአንዳች ማጉብደድ ወይም የጠላቴ ጠላት ወዳጄ ነው ብሎ ካገር ጠላት ጋር የማይሞዳሞድ የቁርጥ ቀን የኢትዮጵያ ልጅ መሆኑን ዳኮታ መስማት አለበት፡፡

ዳኮታ ስለ ትጥቅ ትግልና ስለሰላማዊውም ትግል አስፈላጊነት ማመኑ መልካም ግንዛቤ ነው፡፡ ምናልባት ዳኮታዎች ካልሰማችሁ የኢሕአፓ አቁኣም ሁለ-ገብ ትግልን መከተል ነው፡፡ ሲያመች በሰላማዊ መንገድ ካልሆን ግን ባመጽ (የመሳሪያ) ትግል ነው፡፡ ይህን አቁኣም የያዘው ዛሬ ሳይሆን ገና ከደርግና መኢሶን ጋር ሲፋለም ጀምሮ ነው፡፡ ዛሬ ዳኮታ ልዩ አክብሮት የሚሰጠው ግንቦት 7 በዚህ አቁኣማቸው ኢሕአፓን ጠመንጃ ነካሽ በማለት የብረት ትግሉን ሲያሾፍበት ነበር፡፡ በፓለቲካ አመንዝራ ወንጀል አይደለም ወይ?

ዳኮታ የግንቦት ሰባትና የሻቢያን ጋብቻ እንድናጅብ ያመቻቸናል፡፡የግንቦት ሰባትንና የሻቢያን ጋብቻ የማንደግፈውን ኢትዮጵያኖችን ደግሞ **ቀሽሞች** (ፓለቲካን የብይ ጨዋታ ያህል አሳንሶ)ይለናል፡፡ የ21ኛ ዘመን ሰዎች አንዳልሆን ነው ዳኮታ አድርጎ የሚቆጥረን፡፡ **ያልሰለጠነ ፓለቲከኞች** እንደሚሉን፡፡

ከግንቦት ሰባት በፊት ሕብረ-ብሄር የሆነው የአርበኞች ግንባር ትግሉን ከኤርትራ ለማድረግ ገና ግንቦት 7 ሳይጸነስ እንደጀመረ ይታወቃል፡፡ ዳኮታ የብእሩ ቀለም አዳልጦት ካላስዋሸው በስተቀር ሃቁ ይህ ነው። በኤርትራ ምድር ብሄርተኛ ድርጅቶችም አሉ። እንዲያውም ሻቢያ ለኢትዮጵያ ከቆሙት ድርጅቶች ይልቅ የመገንጠል አባዜ ያላቸውን ብሄርተኛ ድርጅቶች ነው የሚንከባከበው ሲሉ ከአርበኞች ግንባር የወጡ ታጋዮች ሲናገሩ ተደምጠዋል፡፡ ባጠቃላይ ማንም ይሁን ማንም የሻቢያን ድጋፍ መሰረት አድርጎ የሚነሳን ትግልን ብንቃወም በቂ ምክንያት ይዘን ነውና ዳኮታዎች ደንቆሮ አለአዋቂ አታድርጉን፡፡

የሻቢያን ድጋፍ መሰረት አድርገው በምድረ ኤርትራ የሚንቀሳቀሱትን ድርጅቶች እኛ ኢትዮጵያውያን ለምን እንደምንቃወም ዳኮታ ጥናት አድርጎ ሶስት ምክንያቶችን አግኝቶብናል፡፡

1. **"አንድነቷ የተጠበቅ ጠንካራ ኢትዮጵያ እንድትኖር የኤርትራ (ሻቢያ) መንግስት አይፈልግም ወይም ሊፈልግ አይችልም፡፡**

ኢትዮጵያዊው ወገኔ ያላንዳች ጥርጥር ይህ ቀመር ትክክል ስለመሆኑ በሜጋፎን ጮክ ብሎ አባባሉ እውነት ነው ይላል፡፡ ሻቢያ ከተወለደበት ቀን ጀምሮ መቼ ነው የኢትዮጵያ ድንበር የተከበረ እንዲሆን ያገዘበት ጊዜ? የኦሮሞ ነጻ አውጭ፤ የአፋር ነጻ ኣውጭ፤ የኦጋዴን ነጻ አውጭ . . . ወዘተ ሻቢያ የሚያሰለጥነው አንድነትዋን የጠበቀች ኢትዮጵያ እንድትኖር ይሆን? አእምሮን የሚያጎላ መነጽር ቢኖር ኑሮ ሃቁን አጉልቶ እንዲያሳያችሁ በጠቆምኩኣችሁ ነበር፡፡

አንድነትዋ የተጠበቀ ኢትዮጵያ እንድትኖር እዳው ለምንድነው የሻቢያ ወይም የኢሳያስ የምታደርጉት? ሲል ዳኮታ ሊያሸማቅቀን ይሞክራል፡፡ ከኢሳያስ ወይም ከሳቢያ ይህን አይነት እርዳታ የሚመኝ ያለ ካለ ኢትዮጵያዊ ሳይሆን ዳኮት የሚያመልካቸው በምድረ ኤርትራ በርሃ ለኢትዮጵያ ነጻነት ጉድጉኣድ የሚቆፍሩ ህልመኞች ብቻ ናቸው፡፡

በመጀመሪያ ሻቢያ የኢትዮጵያ ጠላት ነው፡፡ የኤርትራ ሕዝብና የኢትዮጵያ ሕዝብ ግን በመካከላቸው አንዳችም የሆነ ጥላቻ የላቸውም፡፡ ሻቢያና የኤርትራ ሕዝብ ሆድና ጀርባ የሆኑትን ያህል የኢትዮጵያ ሕዝብና ወያኔ አንዴም ተገናኝተው አያውቁም፡፡ ሃቀኛ አገርና ወገን ወዳድ ኢትዮጵያውያን የወያኔና የሻቢያ ጠላት ነው፡፡

ሲደመደም አንድነቷ የተጠበቀ ጠንካራ ኢትዮጵያ እንድትኖር የኤርትራ መንግስት(ሻቢያ) አይፈልግም ወይም ሊፈልግ አይችልም የሚለው ቀመር ያለጥርጥር ትክክል ነው፡፡ በመሆኑም ዳኮታዎች መቆጣት አይኖርባችሁም፡፡

## ***መሰረታቸውን ኤርትራ ያደረጉ ድርጅቶች አገራው ጥቅማችንን በማስጠበቅ ረገድ አናምናቸውም***

በመጀመሪያ ሻቢያ ለምንድነው ተቃዋሚ ድርጅቶችን የሚረዳው? ደግ ስለሆነ? ብር ስላለው? ጉራ ስለሚፈልግ? መልሱ ሻቢያ የሚፈልገውን በጫንቃቸው ላይ ሻቢያ የሚፈልገውን ጥቅም ብቻ እንዲሸሙለት ሊጭንባቸው ስለሚፈልግ ነው፡፡ “ይህን ካደረጋችሁልኝ እርዳታ ታገኛላችሁ” ስለሚባሉ የራሳቸውን ጥቅም በመሰዋት የሻቢያን እንደሚያስቀድሙ መታወቅ አለበት፡፡ በሚረዱአቸው መንግስት መዳፍ ስር በመሆናቸው የድርጅታቸውን (አገር ይቅር ለጊዜውና) ጥቅም አያሳልፉ ማለት ዘበት ይሆናል፡፡

ዳኮታዎች በኤርትራ ያሉ ኢትዮጵያዊ ድርጅቶች የፈለገ ቡሆንም በኢትዮጵያ ጉዳይ ላይ ልናምናቸው ይገባል ነው ብሉ የሚምክረን፡፡ የማሞ ቂሎ ታሪክ አይነት!!!!

## 2. አለማቀፋዊ ክልላዊ ጂኦ ፓለቲካ ሁኔታ መሰረት በማድረግ የግንቦት ሰባት አይነት ድርጅቶች መሰረታቸውን ኤርትራ ማድረጋቸው ባሁኑ ጊዜ ጎጂ ነው አያዋጣም አይነት መከራከሪያዎች

ፍሉ (አመታዊ ጉንፋን) ከያዘው መራቅ በሽታው እንዳይዛመትብህ የመርዳቱን ያህል አለም ካወገዘው መንግስት ጋር መተባበሩ አይነቁራኛ ውስጥ ማስገባቱ የተረጋገጠ ነው፡፡ ዳኮታ ይህን ከተጠራጠር ገና የፓለቲካው ሀ ሁ አልተገለጸለትም ማለት ነው ብልን ከማዘን በስተቀር ምን መላ ይኖራል? እንዳናስተምረው ደግም የላቀ ተመራማሪ ነኝ ይለናል አይደል ከወዲሁ፡፡

### ስናጠራቅቅ፡-

አንድነትዋ የተጠበቀ ጠንካራ ኢትዮጵያ አንድትኖር የኤርትራ (ሻቢያ) መንግስት ይፈልጋል አይዞዋችሁ አትጠራጠሩ፡፡ ስለሆነም የግንቦትን 7 ከኤርትራ ትግል መጀመር አትቃወሙ ደግፉ ነው ይምንባለው፡፡ ድሮ ድሮ ገና ሻቢያ መንግስት ሳይሆን ከኢሕአፓ ጋር ልዩነት የፈጠረው የኤርትራ ጥያቄ የቅኝ ግዛት ጥያቄ ነው ብላችሁ ተቀበሉ በማለቱ ነበር፡፡ እንዴታ ጥያቄያችሁ የቅኝ ግዛት ስለመሆኑ አምነናል፡፡ ይህንንም ለሰፊው የኢትዮጵያ ሕዝብ እንዲቀበለው እናደርጋለን አልነበረም ያለው ኢህአፓ፡፡ ዳኮታ ኢሕአፓ ይህን በማድረጉ ቀሼ ነበር ነው የምትሉት? የ21ኛ ዘመን ፓለቲከኛ አልነበረም ነው የምትሉት? መልሳችሁ "አዎ" መሆኑን አውቀዋለሁ፡፡ ግን የሞት ያህል ጥፋት በአገርና በፓለቲካው ላይ እየሰራችሁ ስለመሆኑ ማን በነገራችሁ፡፡

**ሻቢያ ቅድመ ሁኔታ በምድርዋ ላይ ሊደራጁ ለሚፈልጉ አትሰጥም ብሎ ማመን ማሞ ቂሎ መሆን ነው ዳኮታ**፡፡ ሻቢያ የእርዳታ ድረጅት አይደለም ተወደደም ተጠላ፡፡ ጠንካራ ኢትዮጵያ መኖር ለሱዳን ለኬንያ ለሱማሌ ለጅቡቲ ርቀም ለግብጽ አያስፈራም የሚል ሙግት ውስጥ የሚገባ ከሆነ ዳኮታ በውን ተጃጅሏል፡፡ እንዲያውም ዳኮታ እንደ ሱዳን ሱማሌና ኬንያ ከኢትዮጵያ ምድር ይገባኛል ባይ ስለሆኑ አይታመኑም ኤርትራ ግን ሙሉ በሙሉ የምትፈልገው አማጥጣ በማግኘትዋ የይገባኛል ጥያቄ አይኖራትም ይለናል ባድሜንና አሰብን ጥያቄ ዘንግቶ፡፡

ዳኮታ የማይረባ ጥያቄ ጠይቶ የማይረባ መልስ ከመሰንዘሩ ተቆጥቦ **ለምንድነው ሻቢያ ኢትዮጵያዊ ድርጅቶችን ማደራጀት የሚፈልገው**? ለሚለው መልስ ቢሰጥ እመርጣለሁ፡፡

ከኤርትራ ሆኖ መደራጀትን አስመልክቶ አገር ወዳድ ኢትዮጵያዊ አርበኞች ግንባርን በሚገባ ሂስ አቅርበውበታል፡፡ ዛሬ ደግሞ የሞኝ ነገር ሆኖ ግንቦት 7 ለአርበኞች

ግንባር ባልሰራለት መንገድ ላይ መሄድን በመምረጣቸው ሂስ ቢያስነሳባቸው ተገቢ እንጂ የሚያስወቅስ መሆን የለበትም፡፡

ቀና የሆነ የሚረዳ ጎረቤት አገር ቢኖር በተወደደ ነበር፡፡ የትጥቁን ትግል የምጀምርበት አገር አልተገኘምና ትግል ማድረግ አይቻልም ወደሚል ስህተት እንዳንገባ ግን መጠንቀቅ ያለብን ይመስለኛል ዳኮታዎች የምትሰሙኝ ከሆን? የኢትዮጵያ አጎራባች አገሮች ሻቢያን ጨምሮ በሙሉ የወያኔ ወዳጆች ቢሆኑ ትግሉ ይቆማል? ቆርጦ ለሚታገል ጫካው ተራራውና ከጠላት መሸሸጊያው የሚታገልለት ሕዝብ ነውና ከማይሆን የትግል መንገድ ማለትም ከሻቢያ ጋር ከሞዳሞድ መቆጠብ ተገቢ ነው፡፡ ለመሆኑ ኢትዮጵያ ያለአጎራባች አገሮች በውቅያኖስ ላይ ያለች አገር ብትሆን ኑሮ ድርጅቶች የሚወናጨፉበት ጎረቤት አገር ባለመኖሩ ለዘላለም በአድሃሪ መንግስታቸው ተረግጠው መገዛት አለባቸው ማለት ነው ዳኮታ?

የዳኮታ ጥናት ማዕከል "ውሳኔዎች" በሚል ርዕስ ስር ሊለው የፈለገውን አስቐምጧል፡፡ ግን አሳማኝ አይደለም ወይም እሱ ማነውና ውሳኔ የሚያስተላልፍብን የሚል ስሜት ይጭርብናል፡፡ እንዲህ ይላል **"አንዱ ምክንያት ግንቦት ሰባቶች በያዙበት መንገ የሃይል አማራጭ የሞከረ ስላልነበረ ነው. . ."** ጉድ እኮ ነው! አርበኞች ግንባር እኮ ከግንቦት 7 በፊት ኤርትራ ነው ያለው እኮ፡፡ ምናልባት አርበኞች ግንባር ጨሉሌ መሪዎች የሉትም ይሆናል፡፡ ወይም ካንድ ድርጅት ወደ ሌላ ድርጅት የተገለባበጡ እንደነ . . . . አይነት መሪዎች የሉትም ይሆናል፡፡ አርበኞች ግንባር እንደ ግንቦት 7 የብረት ትግሉን አልተቃወሙም ነበር፡፡ የሆነ ሆኖ ግን የአርበኞች ግንባር ሻቢያን ተማምኖ ለትግል መዘጋጀቱ ስህተት ነበር፡፡ በመሆኑም ካስር አመት ሙከራ ያገኙት የሻቢያ ድጋፍ ባዶ መሆኑን ነው፡፡ ይህ ግንቦት ሰባት ካላስተማረስ? ሌላ አስር አመት እንግደልና እንደ አርበኞች ግንባር ......

ምክር ለዳኮታ ጥናት ማዕከል

ስል 60ዎቹ ትግል ሲተረክ ተወደደም ተጠላ በዋናነት የሚጠቀሰው ኢሕአፓ ነው፡፡ ካመራሩ እስከ ተራ አባላቱ የሕይወት መስዋዕት ለአገራቸውና ለሕዝባቸው ሰውተዋል፡፡ ኢሕአፓን ሳይጠቀስ የዚያን ትውልድ ታሪክ ማጥናትና መተረክ አይቻልም፡፡ ይህ ድርጅት ዛሬም መኖሩ ሊያባንናችሁ አይገባም፡፡ በውነተኛነት ለመናገር ኢሕአፓ የሚጠፋው የኢትዮጵያ ሕዝብ የጠፋ እለት ብቻ ነው የሚሆነው፡፡ የኢትዮጵያ ሕዝብ አይጠፋም ዘላለማዊ ነው፡፡ ኢሕ አፓም እንዲሁ!

ተወደደም ተጠላ የኢትዮጵያ ሕዝብ ያለሻቢያ ድጋፍ ነጻነቱን ከወያኔ መዳፍ ፈልቅቆ ይወስዳል።